# ጂቪ ፌዴሬሽኞሹ!

ስም ይወሰድ እንጂ ልብ አይነጠቅም

የመላው ሕዝብ አቋም አይነቃነቅም፤

እንዴት አደራችሁ እንደምን ዋላችሁ

ምሳ እራት ሳትበሉ በታአምር ያላችሁ፤

አንጀትህ ተሰልቦ ሆድህ ተሰልጎ

የሚበላ ጠፍቶ የሚጣድ መገጎ፤

በዛች በባዶ ቤት በጎጆ ተዘግተህ

እግሮችህ ተሳስረው እንዳትለምን ወተህ፤

እየተገላበጥክ በወለሉ ላይ

መጣሁብህ ሲልህ ሞትን አይንህ ሲያይ፤

በመንገድ በታዛው የወደከው ሁሉ

እንደምን ከርመሃል ወገኔ በሙሉ።

አስተዳድር እና ፍትህ እንዲሰፍር

ትናንት እና ወተህ ተናግረህ በምር፤

ልክ እንደ ማእበል ወተህ ትላንትና

ወያኔን ብትነግረው መቼ ሰማህ እና።

ሰላም እና ፍቅር እኔን የራበኝ

አንድነት ነጻነት እኔን የጠማኝ

ተዛዝኖ መኖር ነው እኔን የራበኝ

EthioLion.Com

EthioLion.Com

ሀገሬን ማልማት ነው እኔን የራበኝ

ወያኔ ክፉ ነው ከእንግዲህ በቃኝ።

ብለህ ብትነግረው እንቅጩን በሀቅ

እረሀብ ሆነ መልሱ መቀጫህ እወቅ።

ደግሞ ቅንጅትን የትግልህን አርማ

ነጥቆ ቢወስድብህ ትግልህን ሊያደማ

መላው ኢትዮጵያ አልከው ልብህ አልተቀማ፤

የአንድነቱን ሸማ ለበስከው ወገኔ

ይህንን ሲሰማ ጨንቆታል ወያኔ፤

ስም ይወሰድ እንጂ ልብ አይወሰድም

የተበደለ ሕዝብ ወደኋላ አይሄድም።

የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት

ጎሳና ዘር ሳይለይ የሁሉም ቅንጅት!

የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ይበልጣል

በተባበረ ክንድ ግፈኛን ይቀጣል።

የቆሰለ ልቡን ማንም አይለውጠው

የሚቀምሰው አጥቶ አፈር የሚግጠው፤

በውስኪ በሻምፓኝ ዛሬ ቢቀናጡ

ከታላቅ ከታናሽ ጮማውን ቢቆርጡ፤

በተራበ አጽም ላይ ቆመው ቢደንሱ

አብሮ ለሚጨፍር ለሆዱ ለከርሱ

ቀውጢ ቀን ሲመጣ ይብላኝለት ለእሱ።

ቅንጅት አርማውን መነጠቁን አውቋል

በመላው ኢትዮጵያ ትግሉ በጣም ልቅዋል፤

የመለያ አርማችን ቅንጅት ነበረ

በመላው ኢትዮጵያ ትግላችን ከረረ!

በረሃብ በእርዛት የተጎሳቆለው

በገዛ ሀገሩ ባይተዋር የሆነው፤

በሞት በእስራት በሆዱ ሲቀጣ

ከዚህ የበለጠ ምን መከራ ይምጣ።

ልቡ የበገነው ያረረው አንጀቱ

ሆ! ብሎ ሲነሳ ያኔ ነው መአቱ!

እናንተ ተሻርካችሁ ከወያኔ ጋር ሆናችሁ

የህዝቡን የትቅል አርማ በሸፍጥ ያስወሰዳችሁ፤

የኢትዮጵያ ሕዝብ ያውቃችኋል እከሌ ተከሌ ብሎ አንጠርጥሮ

ነገ ያወጣችኋል በውንፊት አንጓሎና አበጥሮ።

ልብ አይወሰድም ልብ አይሰረቅም

እጅግ የቆሰለ የነፈረ በቂም፤

ሕዝቡ ዝም ብሏል ሲራብም ሲጠማ

ጀግናው ዝም ብሏል ሲታሰር ሲደማ፤

አንገቱንም ደፍቶ አቀርቅሮ እያየ

እየጠበቀነው ቀኑን እየቆየ

ተነስ እስከሚለው ሊክሰው አንድየ።

አንዴ ተግተልትሎ ያቺን ቀን ሲወጣ

ሹምባሽ እና ሙንጣዥ መደበቂያ ሲያጣ፤

ምድሩ ቀውጢ ሲሆን ሲጨልም ቀናቸው

አይን ሲጉረጠረጥ መሄጃ ጠፍቷቸው፤

እንሱን አያርገኝ አዬ ወዮላቸው።

EthioLion.Com

የተራበው ሁሉ በወኔ ሲነሳ

ጀግናው ዳር እስከዳር ሲያገሳ እንደ አንበሳ፤

የመላው ኢትዮጵያ ድምጹ በአንድነት

ምድሩን ሲያናውጠው ወጥቶ በንዴት፤

ሞት ወይም ነጻነት ብሎ ሲገተለተል

ወጥቶ ሲጥለቀለቅ ልክ እንደ ማእበል፤

ታንክ መትረየሱ መድፉ እማይበግረው

የግፈኛ አገዛዝ እጅግ የመረረው፤

የአጨብጫቢው እና የአለቅላቂውን

አይቀርም መያዙ ዘሎ ማንቁርቱን።

ልብ አይወሰድም ልብ አይቀማ

ውስጡ ለቆሰለ አንጀቱ ለደማ።

መላው ኢትዮጵያ ነው አዲሱ ስያሜ

ደግፈው ተነሳ ያሀገሬ ልጅ ደሜ!

ቅንጅትን ለማጥፋት ደክመው ቢያቅታቸው

ስሙን ነጥቀውሃል በውኪሎቻቸው፤

ስም ተወሰደ እንጂ ልብ አይወሰድ

አጭበርባሪው ሁሉ ይቀርባል ለፍርድ፤

በየጓዳው ሆኖ ከመሸረብ ነገር

ወጥቶ መታገል ነው የሚጠቅም ለሀገር፤

ወገንህ ተርቦ በስቃይ ነው እና

በመላው ኢትዮጵያ አድነው ውጣና።

ስም ይነጠቅ እንጂ ይቀጥላል ትግሉ

የመኢአድ መሪ ጀግናው አቶ ኃይሉ!

EthioLion.Com

ከመኢአድ ጋራ ቆመህ በአንድነት

በትግልህ መስርተው አዲሱን ስርዓት!

መሳይ አንድአርጌ - ናሽቪል ተነሲ መኢአድ

ተጻፈ መስከረም አስራ አንድ ቀን ሁለት ሺሕ አንድ ዓ.ም

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኖራለች!

ሞት ለኢትዮጵያ ጠላት!

EthioLion.Com